# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ የምሥራቁ ፈርቀዳጅ

ውድ አንባቢዎች፤ ባለፈው ሳምንት ጽሑፋችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በታዳሽ ኃይል ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ስለመሆኑ በተለይም ደግሞ የንፋስ ኃይል ማመንጫ መጠንን ለማሳደግ ስለሚደረገው ጥረትና ስለአዋጭነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን የሰጡንን ሃሳብ ማስነበባችን የሚታወስ ነው፡፡

በዛሬው ዝግጅታችንም በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል ፈርቀዳጅ ስለሆነው አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ መረጃዎችን ልንሰጣችሁ ወድደናል፡፡ ዛሬም የመረጃ ምንጫችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ናቸው፡፡

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በሱማሌ ክልል የሚገኝ ፈርቀዳጁ የምሥራቅ ኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይል ማመንጫ ነው፡፡ አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ወጪ 257 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን ከዚህ ውስጥ የቻይናው ኤግዚም ባንክ 85 በመቶ የኢትዮጵያ መንግሥት ቀሪውን 15 በመቶ እንዲሸፍኑ ስምምነት ተደርጎ የተጀመረ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በ18 ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል እቅድ የተያዘለት ቢሆንም በዋናነት ከፋይናንስ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች በተባለው ጊዜ መጠናቀቅ እንዳልቻለ ይናገራሉ፡፡ ይሁንና አሁን ላይ አጠቃላይ ሥራው 82 በመቶ እንደደረሰና በውስን አቅሙ ኃይል እያመነጨ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አቶ ሞገስ ለፕሮጀክቱ መጓተት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ሲያስረዱ፤ በአሠራር ደንብ መሠረት ፕሮጀክት ከተጀመረ በኋላ የተሠራው ሥራ እየታየ ለሥራው ማስኬጃ የሚሆን ገንዘብ ይለቀቃል፡፡ በዚሁ መሠረት ከተሠራው ሥራ አንጻር ይከፈል ከነበረው ገንዘብ የተከፈለው ግማሹ ብቻ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ሥራ 82 በመቶ ያህል የደረሰ ቢሆንም የተፈጸመው ክፍያ ደግሞ 40 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ከተሠራው ሥራ አንጻር ክፍያ መፈጸም የተቻለው 50 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ችግሩ የተፈጠረው አበዳሪው ኤግዚም ባንክ በስምምነቱ መሠረት ገንዘብ ባለመልቀቁ ነው፡፡ ያም ሆኖ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በራሱ በኩል እንዲሸፍን ከተያዘለት የገንዘብ መጠን የተወሰነውን በውጭ ምንዛሬ ገፋ አድርጎ መክፈል ስለቻለ ፕሮጀክቱ ወደፊት እንዲሄድ አስችሏል፡፡

በአሁኑ ወቅት እንደ ተቋምም እንደሀገርም እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ስላሉ ፕሮጄክቱ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ የሚገባበት ጊዜ አጭር እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ በአጠቃላይ 48 ተርባይኖች ይኖሩታል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የ32 ተርባይኖች ጀኔሬተር ገጠማ የተጠናቀቀ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 16 ተርባይኖች 40 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት ጀምረዋል፡፡ የተቀሩትም የፍተሻ ሙከራ ሥራዎቻቸው ሲጠናቀቁ ኃይል ማመንጨት እንደሚጀምሩ አቶ ሞገስ አስረድተዋል፡፡

የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ግንባታ ዘርፈ ብዙ ትርጉሞች እንዳሉት የተናገሩት ዳይሬክተሩ ታዳጊ ክልሎች ከሀገሪቱ ሀብት እኩል ተጠቃሚ የመሆናቸውንና የፍትሃዊነት ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ የሚሄዱ መሆናቸውን ማሳያ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እያንዳንዳቸው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ከሀገሪቱ አጠቃላይ ሀብት የመጠቀም መብት አላቸው የሚለውን ድንጋጌ የሚመልስ ነው ብለዋል፡፡ ፕሮጀክቱ አልቆ በሙሉ አቅሙ መሥራት ሲጀምር በተለያየ መልክ በአካባቢው እድገትና ለውጥ ላይ የሚጫወተው ሚና እንዳለም ጠቅሰዋል፡፡ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን



አቶ ሞገስ መኮንን

ለማሳለጥ፣ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት፣ ከጂቡቲ አዲስ አበባ ለተዘረጋው የባቡር ትራንስፖርትና ለደረቅ ወደብ አገልግሎት ከፍተኛ ጥቅም ይሠጣል፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ሰጥቶ የመቀበል፣ ተባብሮ በጋራ የመልማት እንደሆነ የተናገሩት አቶ ሞገስ አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ለምሥራቁ ድንበራችን ቀረቤታ ያለው በመሆኑ ከጎረቤት ሀገራት ጋር አብሮ የመልማት ፍላጎቶችን ለማሳካት በእጅጉ ይረዳል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለጂቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል በሽያጭ እያቀረበች መሆኑን ያስታወሱት አቶ ሞገስ ሱማሌ ላንድና ሱማሊያም ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ የሀገራቱን ጥያቄዎች ለመመለስና ኢትዮጵያም ከሀገራቱ የምትፈልገውን ጥቅም ለማግኘት አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርና ቀጣናዊ ትስስሩን እንደሚያቀላጥፍ ገልጸዋል፡፡

በቀጣይ በሶማሌ ክልል ብቻ አይሻ -1 ፣ አይሻ -3 ፣ አዲጋላ ፣ ቱሉ ጉሌድ፣ ቀብሪ በያህ፣ የመሳሰሉ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችን የመገንባት እቅድ እንዳለ የተናገሩት ዳይሬክተሩ አይሻ-2 ለሚሠሩት አዳዲስ ፕሮጀክቶች እንደ ማሳያ (bench mark) ሆኖ እንደሚያገለግል ተናግረዋል፡፡

ይህ ፕሮጀክት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኢንጂነሪንግ ዘርፍ አዲስ የማማከር አቅም እንዲያገኝ አስችሏል፡፡ ያለፉት ተሞክሮዎቹ እንደሚያስረዱት የሥራ ክፍሉ የማማከር ሥራ የሠራው በኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታና በማከፋፈያ ጣቢያዎች ግንባታ ላይ ብቻ ነበር፡፡ የኃይል ማመንጫ ዘርፉን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ በአማካሪነት የሠራው በአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ነው፡፡ እንደ ተቋም ከዚህ ፕሮጀክት ትልቅ ልምድ እንደተገኘ አቶ ሞገስ ገልጸዋል፡፡

የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ኃይል በማመንጨትም ይሁን በአጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠረውን መዋዠቅ ሊያረጋጉ የሚችሉ መሣሪያዎች ተገጥመውለታል፡፡ ይህደግሞ የተቋሙ የኢንጂነሪንግ ዘርፍ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ አስቀድሞ በመገምገም ባደረገው የማማከር ሥራ የተከናወነ ነው፡፡ በዚህ ሂደት እየተሳተፉ ያሉ ሠራተኞችም ልምድ የሚቀስሙበት የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር የሚያደርጉበት ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል እየተገነባ የሚገኘው የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ የኃይል አቅርቦቱን ከማሳደጉ በተጨማሪ ለክልሉ ኢንቨስትመን መስፋፋት የበኩሉን ሚና እንደሚጫወትም የሚታመን ነው።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ